የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፴
አዲስ አበባ የካቲት ፲፮ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

21st Year No. 30
ADDIS ABABA, 23rd February, 2015


**ማውጫ**


ደንብ ቁጥር ፫፻፵/፪ሺ፯ ዓ.ም
በክብደት ላይ የተመሠረተ ዓመታዊ የተሽከርካሪ ፈቃድ ማደሻ ክፍያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ.......................................................................................ገጽ ፰ሺ፩፻፲፱


**CONTENTS**


Regulation No.340/2015
Axel Load Based Annual Vehicle License Renewal Fee Council of Ministers' Regulation...................page 8119


**የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፵/፪ሺ፯**

## በክብደት ላይ የተመሠረተ ዓመታዊ የተሽከርካሪ ፈቃድ ማደሻ ክፍያን ለመወሰ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፫ አንቀጽ ፭ እና በመንገድ ፈንድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፷፮/፲፱፻፺፱ አንቀጽ ፮ (፩) (ሐ) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "በክብደት ላይ የተመሠረተ ዓመታዊ የተሽከርካሪ ፈቃድ ማደሻ ክፍያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፵/፪ሺ፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 340/2015**

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO DETERMINE AXEL LOAD BASED ANNUAL VEHICLE LICENSE RENEWAL FEE

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No.691/2010 and Article 6 (1) (c) of the Road Fund Establishment Proclamation No.66/1997.

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as the "Axel Load Based Annual Vehicle License Renewal Fee Council of Ministers Regulation No.340/2015".

## ፪.ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፤

፩/ "አዋጅ" ማለት የመንገድ ፈንድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፷፮/፲፱፻፹፱ ነው፤

፪/ በአዋጁ አንቀጽ ፪ የተሰጡ ትርጓሜዎች በዚህ ደንብም ተፈጻሚ ይሆናሉ፤

፫/ "በክብደት ላይ የተመሠረተ ዓመታዊ የተሽከርካሪ ፈቃድ ማደሻ ክፍያ" ማለት ለማናቸውም ተሽከርካሪ በሚኖረው የመጫን አቅም ወይም የመቀመጫ ብዛት እና የአክስል መጠን ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ መሠረት የሚፈፀም ክፍያ ነው፤

፬/ "ተለጣፊ ምልክት" ማለት የተሽከርካሪ ባለንብረት ወይም ባለይዞታ በዚህ ደንብ መሠረት ዓመታዊ የተሽከርካሪ ፈቃድ ማደሻ ክፍያ መፈፀሙን ለማረጋገጥ የሚሰጥ ተለጣፊ ምልክት ነው፤

፭/ "ባለሥልጣን" ማለት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትራንስፖርት ባለሥልጣን ነው፤

፮/ "ቢሮ" ማለት በተሽከርካሪዎች ላይ ዓመታዊ ምዝገባና የቴክኒክ ምርመራ ለማካሄድ በሕግ ሥልጣን የተሰጠው የክልል አካል ነው፤

፯/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፯ (፩) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

፰/ ሰው ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

## 2. Definition

In this Regulation unless the context otherwise requires:

1/ "Proclamation" means the Road Fund Establishment Proclamation No. 66/1997;

2/ the definitions provided for under Article 2 of the Proclamation shall be applicable;

3/ "axel load based annual vehicles' license renewal fee" means a fee levied on any vehicle on the basis of its loading capacity or on the number of seats it has as per the payment schedule attached herewith;

4/ "sticker" means an identification sticker issued to a vehicle owner or possessor to ensure that he has paid the axel load based annual vehicles' license renewal fee in accordance with the provisions of this Regulation;

5/ "Authority" means the Transport Authority of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

6/ "bureau" means any regional body empowered by law to carry out annual registration and technical inspection of vehicles;

7/ "region" means any state referred to in Article 47(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes the Addis Ababa and Dire Dawa City Administrations;

8/ "person" means any natural person or juridical person;

፱/ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ፆታ ይጨምራል፤

## ፫. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ ደንብ በሕግ በግልፅ ተለይተው ተፈጻሚ እንዳይሆንባቸው ከተደረጉት ተሽከርካሪዎች በስተቀር በማንኛውም የኢትዮጵያ መንገዶች ላይ በሚንቀሳቀሱ ማናቸውም ተሽከርካሪዎች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

## ፬.ስለክፍያ

፩/ የማናቸውም ተሽከርካሪ ባለንብረት ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ በተመለከተው ታሪፍ መሠረት ዓመታዊ የተሽከርካሪ ፈቃድ ማደሻ ክፍያ መክፈል አለበት፤

፪/ በዚህ ደንብ መሠረት መከፈል ያለበት ክፍያ ያልተፈፀመለትን ተሽከርካሪ ይዞ የተገኘ ማንኛውም ባለይዞታ ወይም አሽከርካሪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር (፩) የተመለከተውን ክፍያ መክፈል አለበት።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) መሠረት ክፍያ ከተፈጸመ በኋላ ባለሥልጣኑ ወይም ቢሮው ለባለንብረቱ፣ ባለይዞታው ወይም አሽከርካሪው ክፍያ በተፈፀመለት ተሽከርካሪ መለያ ቁጥር ስሌዳ አንድ ተለጣፊ ምልክት ይሰጠዋል::

## ፭.ተለጣፊ ምልክትን ስለመያዝና ስለማሳየት

፩/ ከፊት የንፋስ መከላከያ መስታወት ላላቸው ባለሞተር ተሽከርካሪዎች የተሰጠው ተለጣፊ ምልክት ከመስታወቱ ላይ በታችኛው የቀኝ ማዕዘን ተለጥፎ መታየት አለበት::

፪/ ከፊት የንፋስ መከላከያ መስታወት ለሌላቸው ባለሞተር ተሽከርካሪዎች የተሰጠው ተለጣፊ ምልክት በማንኛውም ጊዜ ተሽከርካሪውን በሚነዳው፣ በሚያንቀሳቅሰው ወይም በሚያስጠግነው ሰው እጅ መቀመጥ አለበት::

9/ any expression in a masculine gender includes the feminine gender.

## 3. Scope of Application

This Regulation shall be applicable on any vehicle operating on any Ethiopian roads, except those explicitly excluded by law from the application of this Regulation.

## 4. Fee

1/ Any owner of a vehicle shall pay axel load based annual vehicles' license renewal fee in accordance with the tariff attached herewith.

2/ Any possessor or driver who operates a vehicle for which axel load based annual vehicles' license renewal fee was not discharged shall be subject to pay the fee pursuant to sub-article (1) of this Article.

3/ The Authority or bureau shall issue a sticker to the owner, possessor or driver with reference to the identification number plate of the vehicle for which fee is paid in accordance with sub-articles (1) or (2) of this Article.

## 5. Possession and Display of a Sticker

1/ The sticker issued for motor vehicles having windscreen shall be displayed being affixed on the right side of its windscreen lower corner.

2/ The sticker issued for motor vehicles having no windscreen shall always be kept with the person driving, operating or maintaining the vehicle any time.

፫/ ለተሳቢ ወይም ግማሽ ተሳቢ የሚሰጥ ተለጣፊ ምልክት በጎታቹ ባለሞተር ተሽከርካሪ መስታወት ላይ በታችኛው የቀኝ ማዕዘን ይህንኑ ተሳቢ ወይም ግማሽ ተሳቢ ከሚጎትተው ባለሞተር ተሽከርካሪ ከተሰጠው ተለጣፊ ምልክት ጐን ተለጥፎ መታየት አለበት፡፡

## ፮.ስለክፍያ አሰባሰብ

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፮(፬) በተደነገገው መሠረት ባለሥልጣኑ ወይም ቢሮው ወይም እነርሱ ውክልና የሚሰጡት አካል ማናቸውም ተሽከርካሪ ለዓመታዊ የቴክኒክ ምርመራና ምዝገባ ሲቀርብለት ከዚሁ ተሽከርካሪ ሊሰበሰብ የሚገባውን ዓመታዊ የተሽከርካሪ ፈቃድ ማደሻ ክፍያ መሰብሰብ አለበት።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተሰበሰበ ክፍያ በአንድ ወር ውስጥ ወደ መንገድ ፈንድ የባንክ ሂሣብ ገቢ መደረግ አለበት፡፡

## ፯. ተለጣፊ ምልክት ስለማዘጋጀት እና የአገልግሎት ዘመን

፩/ በባለሥልጣኑ፣ በቢሮው ወይም እነርሱ በሚወክሉት አካል በኩል አገልግሎት ላይ የሚውሉትን ተለጣፊ ምልክቶች እና የክፍያ መሰብሰቢያ ደረሰኞች አዘጋጅቶ የሚያሠራጨው የመንገድ ፈንድ ጽህፈት ቤት ነው ፡፡

፪/ የተለጣፊ ምልክት ከተሠጠበት ቀን አንስቶ ለአንድ አመት ብቻ የሚያገለግል ይሆናል፡፡

## ፰. ተለጣፊ ምልክት ስለመኖር

፩/ ተሽከርካሪን የሚነዳ፣ የሚያንቀሳቅስ ወይም የሚያሠራ ሰው የተሽከርካሪውን ተለጣፊ ምልክት እንዲያሳይ በትራፊክ ፖሊስ ወይም በሌላ ሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል ሲጠየቅ ወዲያውኑ ማሳየት አለበት፡፡

3/ The sticker issued for trailer or semi-trailer shall be displayed being affixed besides the sticker issued for the motor vehicle which draws the trailer or semi-trailer on the right side of the windscreen's lower corner.

## 6. Collection of Fee

1/ In accordance with sub-article (4) of Article 6 of the Proclamation, the Authority or bureau or other bodies delegated by them shall collect axel load based annual vehicles' license renewal fee from any vehicle that appears for annual technical inspection and registration.

2/ The fee collected pursuant to sub-article (1) of this Article shall be deposited in the road fund bank account within a month.

## 7. Preparation and Validity of Sticker

1/ The Road Fund Office shall prepare and distribute the sticker to be used by the Authority, bureau or other bodies delegated by them and the receipts to collect fee.

2/ A sticker shall be valid only for one year from the date of its issuance.

## 8. Absence of a Sticker

1/ Any driver, operator or a person who maintains a vehicle shall immediately show a sticker upon the request by a traffic police or by any other person authorized to do so.

፪/ የተሽከርካሪው ባለቤት ወይም ባለይዞታ ክፍያ መፈጸሙን እስኪያረጋግጥ ድረስ ትራፊክ ፖሊስ ተሽከርካሪውን በቁጥጥር ሥር አውሎ በሥራ ሰዓት የተያዘ ከሆነ ከስድስት ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ፣ ከሥራ ሰዓት ውጪ የተያዘ ከሆነ እንደሁኔታው ከአስራ ሁለት ወይም ከሃያ አራት ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ተሽከርካሪው በተገኘበት ክልል ለሚገኘው ክፍያ ሰብሳቢ ባለሥልጣን ወይም ቢሮ ያቀርበዋል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት በቁጥጥር ሥር የዋለው ተሽከርካሪ የሚለቀቀው በዚህ ደንብ የተወሰነውን ክፍያ ተፈጽሞ ተለጣፊ ምልክት ሲሰጠው ወይም ክፍያውን የፈፀመ ለመሆኑ የሚያስረዳ ማስረጃ ሲያቀርብ ይሆናል።

**፱. ምትክ ተለጣፊ ምልክት ስለመስጠት**

ተለጣፊ ምልክት የጠፋ፣ የተሰረቀ፣ የተቀደደ፣ የተበላሸ ወይም የማይነበብ የሆነ እንደሆነ፣ የተሽከርካሪው ባለንብረት ወይም ባለይዞታ ምትክ ተለጣፊ ምልክት እንዲሰጠው ለባለሥልጣኑ ወይም ለቢሮው ወይም በእነርሱ ለተወከለው አካል ሲያመለክት ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተመለከተውን ክፍያ ሲፈጽም ምትክ ተለጣፊ ምልክት ይሰጠዋል።

**፲. ደንብ መተላለፍ**

ይህን ደንብ ተላልፎ የተገኘ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው የደንብ መተላለፍ ድንጋጌ መሠረት ይቀጣል፡፡

2/ The traffic police shall seize the vehicle until he verifies payment of fee by the driver, operator or a person who maintains vehicle and shall bring such vehicle to the Authority or bureau which collects fee within six hours from the time of its seizure if it is seized during working hours, or within 12 hours or not more than 24 hours if it is seized out of working hours, as the case may be.

3/ The vehicle so seized shall be released only upon the payment of fee and issuance of sticker or upon producing evidence showing payment of fee.

**9. Issuance of Replacement Sticker**

The Authority or Bureau shall issue a replacement sticker to an owner or possessor of a vehicle, whose sticker has been lost, stolen, mutilated, destroyed or has become illegible upon application to this effect and payment of the fee determined for this purpose under the schedule attached herein.

**10. Petty Offence**

Any person who violates the provisions of this Regulation shall be Punishable in accordance with the applicable provisions of relevant regulation.

፲፩. <u>ደንቡ ስለሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

**አዲስ አበባ የካቲት ፲፮ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሣለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

11. <u>Effective Date</u>

This Regulation shall come into force on the Date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 23rd day of February, 2015.**

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

## <u>ክብደት ላይ የመሠረት ዓመታዊ የተሽከርካሪ</u>
## <u>ፈቃድ ማደሻ ክፍያ ታሪፍ</u>

| ተ.ቁ | የተሽከርካሪ ዓይነት ወይም የመጫን አቅም | የዓመታዊ ክፍያ መጠን /በብር/ |
|---|---|---|
| **፩** | **አውቶሞቢሎችና የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች** | |
| ፩.፩ | እስከ ፭ መቀመጫ ያላቸው | ፩፻፳፭ |
| ፩.፪ | ከ ፮ እስከ ፲፪ መቀመጫ ያላቸው | ፩፻፶ |
| ፩.፫ | ከ ፲፫ እስከ ፳፱ መቀመጫ ያላቸው | ፪፻ |
| ፩.፬ | ከ ፴ እስከ ፵፬ መቀመጫ ያላቸው | ፪፻፶ |
| ፩.፭ | ከ ፵፬ በላይ መቀመጫ ያላቸው | ፫፻ |
| **፪** | **የደረቅ ጭነት ማመላለሻዎች** | |
| ፪.፩ | እስከ ፲፭ ኩንታል የሚጭኑ | ፫፻ |
| ፪.፪ | ከ ፲፮ እስከ ፴፭ ኩንታል የሚጭኑ | ፭፻፶ |
| ፪.፫ | ከ ፴፮ እስከ ፸ ኩንታል የሚጭኑ | ፩ሺ |
| ፪.፬ | ከ ፸፩ እስከ ፩፻፳ ኩንታል የሚጭኑ | ፩ሺ.፭፻ |
| ፪.፭ | ከ፩፻፳፩ እስከ ፩፻፹ኩንታል የሚጭኑ | ፪ሺ. |
| ፪.፮ | ከ ፩፻፹ ኩንታል በላይ የሚጭኑ | ፪ሺ.፭፻ |
| **፫** | **የፈሳሽ ጭነት ማመላለሻ** | |
| ፫.፩ | እስከ ፲ሺ. ሊትር የሚጭኑ | ፮፻፶ |
| ፫.፪ | ከ ፲ሺ.፩ እስከ ፲፫ ሺ. ሊትር የሚጭኑ | ፩ሺ.፪፻፶ |
| ፫.፫ | ፲፫ ሺ.፩ እስከ ፲፬ ሺ. ሊትር የሚጭኑ | ፩ሺ.፭፻ |
| ፫.፬ | ከ ፲፬ ሺ. ሊትር በላይ የሚጭኑ | ፪ሺ. |
| **፬** | **ሌሎች** | |
| ፬.፩ | ሞተር ሳይክሎች | ፶ |
| ፬.፪ | ልዩ ተንቀሳቃሽ መሣሪያዎች ወይም ከመንገድ ውጪ የሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎች | ፫፻ |
| **፭** | ምትክ ተለጣፊ ሲሰጥ | ፩፻ |

**TARIFF ON ANNUAL VEHICLES LICENSE RENEWAL FEE BASED ON AXEL LOAD**

| No. | Vehicle Type & Loading Capacity | Annual Fee (Birr) |
|---|---|---|
| 1 | **Automobiles and Public Transport Vehicles** | |
| 1.1 | Up to 5 seats | 125 |
| 1.2 | 6 up to 13 seats | 150 |
| 1.3 | 13 up to 29 seats | 200 |
| 1.4 | 30 up to 44 seats | 250 |
| 1.5 | Above 44 seats | 800 |
| 2 | **Freight Trucks with a Loading Capacity** | |
| 2.1 | Up to 15 Quintals | 300 |
| 2.2 | 16 up to 35 Quintals | 550 |
| 2.3 | 36 up to 70 Quintals | 1,000 |
| 2.4 | 71 up to 120 Quintals | 1,500 |
| 2.5 | 121 up to 180 Quintals | 2,000 |
| 2.6 | Above 180 Quintals | 2,500 |
| 3 | **Fuel/Liquid Loading Trucks with a Loading Capacity** | |
| 3.1 | Up to 10,000 Liters | 750 |
| 3.2 | 10001 up to 13,000 Liters | 1,250 |
| 3.3 | 13,001 up to 14,000 Liters | 1,500 |
| 3.4 | Above 14,000 Liters | 2,000 |
| 4 | **Others** | |
| 4.1 | Motorbikes | 50 |
| 4.2 | Special-Mobile equipment (Off-road operating vehicles) | 300 |
| **5** | **Issuance of Replacement sticker** | 100 |

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት